# የለንደኗ ደብረ-ጽዮን ማርያም
# አለቃ ለነበሩት
## የመጨረሻ ማሳሰቢያ ብሎም ማስጠንቀቂያ

## ውጪ ያለነውን ኹሉ ማሰባሰቢያ!

ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ

መጋቢት ፲' ቀን ፪ ሺህ ፭

## የመጨረሻው ማሳሰቢያ

*በቤተክርስቲያናችን አስተዳደር ላይ በአጠቃላይ በወረደው መዓትና በልጆቿም ላይ በሚጎርፈው ሰቆቃ እንጀታችን ያረረው፦ ቆሽታችን የደበነው ልጆችዋ ብቻ ሳንኾን የሌሎች ዕምነት ተካታዮችም ናቸው/ናችሁ። ሰዎች ናችሁና የሚሰቃዩትም ወንድሞቻችሁ ናቸውና! ለዘመናት ከኖሩበት አርሰው ቡቃያቸውን እያዩ የሚሰበስቡትን ምርት በማሰብ ተስፋቸው ያቀጠቀጠላቸው....ባውሬዎች እንደአውሬዎች በውድቅት እየተባረሩ መውደቂያ ስላጡት ጎሊናችን አላስቀምጥ ያለን ጥቂቶች አይደለንም። ባጠቃላይ በኢትዮጵያውያን ልጆቻችን ላይ በየበረሀውና በየሰዉ አገር በከፋ ውርደትና ስቃይ ከሞተ በላይ እንዳሉ እያየን የሚሰማንን እያንዳንዳችን እናውቀዋለን። ዐቅመ-ደካሞች በመኾናችን 'ለደካሞችም ኃይል ነኝ፡' ወዳለው አባታችን ለመጸለይ እንሞክራለን። ይህ ኹሉ ከተነገረው መፈጸም ላይ ያለ ነው።*
*ሉቃስ ም ፲፰ ከቁ፡2 ጀምራችሁ ስታነብቡ፦*
*"በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ።" ለኛ ለቤተክርስቲያኗ ልጆች፦ እንዲሁም መላ ጉዳዩን ለሚሰሙ ፦ ኢትዮጵያውያን ሃፍረት ያላበሰን ከላይ የተጠቀሰው 'ዳኛ!' ለቤተክርስቲያናችን ያገለግላሉ መነኩሴ ናቸው ብሎ መርጦ ደመወዝ ቆርጦ የቀጠራቸው ሰው ናቸው። ታሪኩን አልደጋግመው።የጥቂት ካህናት ግብረ-አበሮች እንዳሉ ግን መጠቀስ አለበት።*
*ካለፈው ጽሑፌ በኋላ ከተፈጸሙት ወንጀሎች አንዳንዱን ልጥቀስ፡፤ ከሩቅ ያለውን ወገን ለንደን ባለነው ላይ 'እንዴት በቤ/ክን ይህ ኹሉ ይደረጋል?!' በማለት በመቆረቆም ቢኾን፦ እንዳይፈርድ ወገንን ከስህተት ለማዳን እነሆ!*
*--ዐቢይ ጾም በጀመረ ዕለት የተጨነቀው ሕዝብ 'ኃይል የለኝም ኃይል ኹነኝ!' ለማለትና ለመማጸን ደክሞ እገዛው ቤ.ክን ቢሄድ አምላኩንም እኔን ያገለግላል ብሎ የቀጠረው*

# "ላልተወሰነ ጊዜ ተዘግቷል!"

ብሎ አሸገው

*የታከለው ሰበብ ከአገሪቱ ሕግጋት ጋር የሰላምታ ዕውቀት እንኳን የሊለው ነው።*

- ከሰዓት በኋላ በመሪጌታውና በዲያቆን ታጅበው ኤምባሲ ሄደው

# “ቁልፉን ለማስረከብ ዝግጁ ነኝ!”

‘አሉን’ ሰማን (ምልልሳቸውን እንለፈው)

- በማግሥቱ ስብሰባ ላይ ‘ቁልፉን ለአዲስ አበባው ሲኖዶስ ላስረክብ ዝግጁ ነኝ’ ብለው መደንፋታቸው ደረሰን።
- አንድ ጳጳስ እኛ ዘንድ መጥተው የጳውሎስ ስም እንዲጠራ ቢሉ እንደማይኾን ተነግሯቸው ለአውሮፓ ሊ.ጳ. መንበር ሊያደርጓት የተመኗትን አጥተው በጥገኝነት ከምታገለግል ቤ.ክን ተጠግተው ይኖራሉ። በስራቸው የሚተዳደሩ የአሥራ ሰባት ያህል የአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ወኪሎች በተገኙበት መጋቢት ፳ ቀን እሁድ ተሰብስበው የቤተ ክርስቲያናችን አለቃ የነበሩት አኹንም ቁልፍ ለማስረከብ ዝግጁነታቸውን በኩራት ገልጸው የተመካከሩትን ሰማን፦ አኹንም ዝርዝሩን እናቆየው። ጳጳሱም እኛ እያለን ኢምባሲ ለምን ሄድህ ብለው ዘለፉ እንዳተረፉም ሰማን።

0 የቅበላ እሁድ ዕለት አብዛኛው መእመን “አባ ቁልፋችንን ያምጡ- ያስረክቡ!” እያለ በምሬት ሲጮህ አባ በስርቆሽ በር ሄዱ። ከቀሩት ካህናት ጋር በመወያየት ከካህናትና ከምእመናን አቻ ቁጥር ያላቸው ተዳራዳሪዎች (ያለ አባ!) ለማግሰኞ ተቃጠሩ። ካህናቱ “አንመጣም!” እንኳን ሳይሉ ቀሩ።

የጌታ ቃል በሮሜ ምᎯ፦ ከቁ ᎐᎙፦ እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ ዐእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው።… እባካችሁ እስከ ቁ ፴፪ ድረስ ዝለቁት። የቀድሞው አለቃ ጉዳይ ይህ ኾነ። ያሳዝናልም! ከረቂቁ ጀምሮ እስከ ቤተክርስቲያን መዝጋት ሲደረስ የቃሉን መፈጸም አያሳይም?

በቤተክርስቲያኗ ባለቤቶችስ በኩል? መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል በተመረጡት አራት ምእመናን በሙሉ ትእግሥትና በሳልነት አርቆ አስተዋይነትም ከጠበቆች ጋር በመመካከር በተደፈርን “ እሽጉን ቀድደን-ቁልፉን ቀይረን …” ባረረ፣ በደበነ ግለት ‘ባለቤትነታችንን እናረጋግጥ ወዘተ’ ሲባል እያበራረዱ ሥራችን እንደቀጠለ ነው። ልብ ቢሰጣቸው ራሳቸውን በኅሊና ለፈጣሪያቸው ለማስገዛት ይችሉ/ይሞክሩ እንደኾን ተስፋ ባለምቁረጥ በምሳሌዎች ልሞክር።

አዲስ አበባ ሲመላለሱ ባለሥልጣኖች ዘንድ ይገቡ እንደነበር ይነገራል። ምናልባት በነዚህ ጊዜያት “አስረክባለሁ” ብለው ለርሳቸውም ጽጽስናን ቃል አስገብተው ከኾነ፦ ለጌታ የገቡትን ቃል ከማፍረስ ወይ ለሰው የገቡትን? የትኛው ይቀልል እንደኾን አላውቅም። ለዚህ መልስ ርሳቸው ይሻላሉ!! ምርጫቸውን ያውቃሉና።

በጥቅምና ለጌታ በገቡት ቃል መኻከል ቅራኔ ሲፈጠር አንድ በአኹኑ ጊዜ የቤ/ክኑ አስተዳዳሪ ከነበሩት በዕድሜ ብዙ የሚራራቅ ዓለማዊ የልብ ወዳጄ የመረጠውን ላውጋችሁ። ምናልባት እዚህ ከተደረሰም በኋላ ከቃል ማክበር ጋር ያገናኝ እንደኾን በማለት ነው። ወዳጄን ‘ተስፋ አይቆርጤ!’ ልበለው። ባሕርዩን ይገልጸዋልና!

ተስፋ አይቆርጤ አገሩ እያለ መንግሥቱ ‘አደገኛ ናቸው፡፤ ተናግረው ያሳምናሉ…ስለዚህ ቁጥጥራችን ውስጥ እናስገባቸው” እያለ ቢወተወትም ጓዶቹ ተስፋ አይቆርጤ ለውጥ ፈላጊ መኾኑን በማስረጃ እያስደገፉ ሊያቆዩት መቻላቸውን ያውቅ ነበርና አንድ ቀን መንግሥቱ ማሸነፉ አይቀርም በማለት ሊሰደድ ቀረጠ። መውጫው ቀላል አልነበረም። ስለዚህ ወደፈጣሪው ‘አውጣኝ እንጂ ለአንድ ዓመት አገሬ የምትድንበትን መንገድ ስፈልግ ለምኜም ቢኾን እጥራለሁ!’ ሲል፦ ለፈጣሪውም ሲናገር ምሥጢሩ በርሱና በፈጣሪው መኻከል ብቻ ነበር። የማይሳነው አምላክ በስብሰባ አድርጎ እንዲወጣ አስተካከለለት። ይህ የጭፍን ነገር አልነበረም መኳንንት ለንደን ላይ

ድርጅት ለማቋቋም ዝግጅት ላይ እንደነበሩ መጥቶ አይቶ አነጋግሮም ነበርና! ስለዚህ የሚቋቋመው ድርጅት አቋቁሞኝ ጫካ እገባለሁ በሚል ነበር። አልኾነም!
ለማንኛውም ዠኔቭ ለቀይ መስቀል ጠ.ጉ ጥቅምት ፱ ቀን ፷፰ ዓም ወጥቶ ስብሰባ ላይ እንዳለ፦ አንድ በየስብሰባዎች ሲመጣ የሚያያቸው፦ ለ'ሰላም-ሰላም' ያህል የመተዋወቅ ደረጃ የነበረው፦ ባለባበሳቸው ዓይን የማይገቡ ሽምግል ያሉ ሰው፡ መጥተው 'እባክህ ነገ ምሳ ልጋብዝህ' አሉት። ተስፋ አይቀርጤም በደስታ ተቀበለ። ቀጠል አርገው 'ሬሶራንት ይኹን ካፌቴሪያ?" አሉ። ኹለተኛውን መርጦ በቀጠሯቸው ሲገናኙ፡፤ "ለመኾኑ ካፌቴሪያን ለመን መረጥህ?" አሉት? ፈተና ኖሯል።
ይህን ያህል ጊዜ ስመላለስ ውድነቱን በመስማቴ አልሞከርሁትም። አኹን ብሂድ ብዙዎቹን ተሰብሳቢዎች ስለማውቃቸው፦ ጥያቄ ውስጥ ልገባ አልፈለግሁም፦ አላቸው። ሲል 'ዐዋቂነት ነው ብለው ተቀበሉት። ጃንሆይን ነሐሴ ገድለው ጥቅምት ስለወጣ ያገራችን ጉዳይ ትኩስ ነበርና ስለአገር በደምብ የምርመራ ያህል ጠይቀው መጨረሻ ላይ ታዲያ ልትመለስ ታስባለህ? አሉት፦ በአሉታ መልሰ።በዚህ ጊዜ ነበር ማንነታቸውንና ምንነታቸውን የገለጹለት። እሱም ከመጣባቸው ስብሰባዎች ለሦስት ወራት ያህል የቆየበት እንደ 'የተ.መ. የባሕሮች ሕግ ስብሰባ አንዱ ነበር።

ለተ.መ.የዠነቭ ጽ/ቤት የአስተዳደር ኃላፊ መኾናቸውን፦ ዋናውም ግዳጃቸው

"Talent hunting is my primary duty & responsibility. The UN is an intricate organization and it needs highly talented personalities. That is why you see me going from committee room to committee room. Such meetings are my hunting grounds. I even go to non UN conferences like The Red Cross.'

ከዚህ በኋላ ያላቸው ሥልጣን የሚፈቅድላቸውን ከፍተኛ ደረጃ ያለው ሥራ ሊሰጡት እንደሚፈልጉ ነገሩት። ቃሉን በተመለከተ የመጀመሪያው ፈተናው ኾነ። ከልብ አመስግኖ እንደማይችል ነገራቸው። ለምን ሲሉም አስረዳቸው። እድሜና ሥራ ብዙ ያሳያቸው አዛውንት፦ የስደትን ክፉነት ዘርዝረው ካስረዱት በኋላ፦ 'እንደማስበው' አሉ ፤- ቆየት ብለው እንደገና 'እንደማስበው፦ የበለጠ መራሩ ነገር ስደት መቼ እንደሚያልቅ አለመታወቁ ነው።' አሉና

- ክርስቲያን ነህ?
- አዎን፡
- ኦርቶዶቅስ ነህ?
- አዎን፡
- እኔም ኦርቶዶቅስ ነኝ። ግሪክ ኦርቶዶቅስ። አኹን ወዙን ላለማሳጣት እንደገና በተናገሩበት ቋንቋ ልጻፈው።
- Our religion is neither harsh nor cruel. You don't have to keep the vow word for for word, letter by letter. Our 𝒢od is our Father. Even earthly fathers are understanding and forgiving. Therefore; you can give money to your church and the poor instead of what you intended..

ተስፋ አይቀርጤ፦ እንኳን ሊቀበል አልጓጓም። የእናት አገሩና የወገኑ ሥቃይ፡ ስንኳን የርሱን የቤተሰቡን ኃላፊነት እንዲያስቀድም አላደረገውም። በዚያን ጊዜ ወደ አርባው ቢኾን ነው።

አለቃችን የነበሩት መነኩሴ ነኝ ብለዋል። የመነኩሴ ቆብም ደፍተዋል። ከመመንኮስ በፊት አርባ ቀን አርባ ሌሊት ጉድጓድ ውስጥ ብቸኝነትን ይችሉ እንደኾን የመፈተኛ ጊዜ እንደነበረ ከጳጳሳት ሰምቻለሁ። ከዚያ በኋላ ነው ለዚህ ዓለም ሹመት-ጥቅም-ገንዘብ ወዘተ

“ሙትነኝ” ብለው በመሃላ ተገንዘው እንደሞቱ ተቆጥሮ ተዝካር የሚወጣላቸው። ከዚህ በኋላ ምድራዊው ሕይወታቸው ለክርስቶስ ማገልገል ብቻ መኾኑን የሚምሉት። በዚህ ዓይነት የክርስቶስ አገልጋይነታቸውን ለማንም የሚያሳይ አለባበስና ቆብም የሚደፉት።ይህንንም በማመን ነበር የለንደኑ ምእመን ለፍቶ ደክሞ ለአሮጊት እናቱ ለሕሙም ወንድሙ ከሚልከው ቀንሶ በአንድ ሚሊዮን ከሰባት መቶ ሺህ ፓውንድ የገዛውን ሕንጻ በቤተክርስቲያንነት ያጠናክሩልኛል። ልጆቼን በሃይማኖታቸው በባህላቸው ያሳድጉልኛል ብሎ መርጦ በጥሩ ደመውዝ በራሱ ላይ የሾማቸው።
ዝርዝር ሳልገባ አንድ በአሜሪካን አገር በሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድሃኔዓለም ቤተክርስቲያን ውስጥ የተፈጠርውን ለአብነት ያህል ልጥቀሰው። ዘ-ሐበሽ ከሚል ትናንት ከወጣ ድረ-ገጽ የተገኘ ነው። ሲመስጡ አባ ፍቅረ ማርያም የሚባሉ አንገታቸውን የደፉ የዕውነተኛ መነኩሴ ገጸ-ባሕርይ የሚታይባቸው ነበሩ። ምእመኑ ከየትኛውም ሲኖዶስ ጋ መወገን አለመፈለጉን አስረግጦ ርሳቸውም አምነው የአስተዳዳሪነትም ሃላፊነት ይዘው ሲሠሩ ወደ አዲስ አበባ ይሄዳሉ። ጸጽሰው የጳውሎስ ሎሌ ኾነው ይመሰሱና በአደራ የተቀበሉትን ቤተ/ክን ለሃይማኖታችን አጥፊዎች ሊያስረክቡ ይፈልጋሉ። ጸሐፊው “…ከይሁዳዎች መጠበቅ የኹላችንም ኃላፊነትም ግዳጅም ነው!” በሚል ርዕሱ “ ይህ የሚያሳየው ለአባላት የሚሰጡትን ዝቅተኛ ክብር ነው!” ይላል። ይህ ይባል እንጂ በምንኩስናቸውም ኾነ በሌላው ስነምግባር በአሉታ ሲጠቀሱ አልተሰማም፡፤ ይህም እፎይ! የሚያሰኝ ነው። ውርደታቸው ውርደታችን ነውና!! ከዚች ስሜት ጋ እኛስ የለንደኖቹ እንተዋወቃለን?      የሚኒሶታው ከተሾሙ በኋላ ነው፦ የለንደኑስ? እንዴሾሙ?
እስቲ ወደ ዠኔቩ ምሳሌ ልመልስና አንድ ተራ ምእመን የጌታችንን ቸርነትና መሃሪነት ሲያስተምር የኛ መነኩሴ እንዴት ያጡታል።
እንግዲያውማ አንድ ተራ መእመን ስለአምላካችን መሃሪነት ያስተማረውን የቤ/ክርስቲያኔ መነኩሴ ነኝ የሚሉት አያውቁም ለማለት እንዴት ይቻላል?
ውሸትን እምነታችን ይከለክላል፤፡ አለቃችን ለነበሩት ግን “ያፍ ዳገት የለውም!” እንድሚባለው ነው፤፡ ተቆጥሮ በማያልቅ ኹናቴ። ዋሽቶ ማጣላት ክፉ ነው ርካሽ ነው! ቅዱስ መጽሐፍን ግን በውሸት በመጥቀስ ሰውን ማጣላት በተለይም ወጣትን ማሳሳት በሰማይም በምድርም ያስጠይቅ የለ? ሐዋርያት ከትምሕርት/ጸሎት በኋላ የተገኘውን ካለው ሰው ጋር ሊቅ ከደቂቅ ሳይሉ አብረው ሲካፈሉ መግባባትን የማስፈኚያ ፍቅርን የማዳበሪያ አድርገውት ሥርዐቱ ‘አጋፖ’ ?ይባላል።በግሪክኛ ፍቅር” ማለት ነው። የኛዎቹ ግን አዛውንት እናቶች ሕጻናት የሚያምመውም ኾነ ደህናው በሐሩርም ኾነ በውርጭ ሲቀጣ ( ለዚሁ ስብሰባ) መዘምራኑንና ዲያቆናትን በሀሰት ወሬ ለጥላቻ መስበኪያ ይዳርጓቸዋል። አያቶቻቸው የሚሔኑትን በመሳደብ ሳያውቁ ራሳቸውን ያዋርዳሉ። ካህንናቱም “ተዉ!” ሲሉ ተደምጠው አይታወቅም። “ቹ!” ባዮቹ ናቸዋ! እዚህ ላይ ማርቆስ ም 9 ከቁ 42 — 50 እንድታነብቡ ስጋብዝ የመጀመሪያውን እዚህ ላስነብብ።
“በኔም ከሚያምኑት ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ኹሉ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር…”
ስለዚህ ልጆቻችንን የማዳን ግዴታ ስላለብን አስቀድመው ካህናት ለልጆቹ ዕውነቱን ነግረው ይቅርታ ጠይቀው ከታላቅ ሃይማኖታዊና ባህላው ጥፋት ይመልሷቸው።
በትልልቆቹ ላይ ስለተፈጸመው ላልፈው ስፈልግ ልክ እንደልጆቹ በአጠቃላይ ‘ምሥጢር ተደፈረ - ቃለ ዐዋዲ ተጣሰ - ቀኖና ፈረሰ” ብለው በሀሰት ከምእመናን መጽሐፍ ቅዱስን ብዙ የማያነብቡትን ማወናበዳቸው ቢጸጽታቸው ይቅርታም ቢጠይቁ፦ ደግ። ባይጠይቁ.. ከጉዳዩ ጋር በአጋምም በቀጋ የማይገናኙ ጥቅሶችን በመጻፍ በማስመሰል ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰ በማለት ብቻ እንዲሳሳቱ በማድረጋቸው ጸጸታቸውን ቢገልጹ እንደሚጠቅም ላሳስብ እወድዳለሁ።  ባያደርጉትም እንዳሻቸው። መጋለጣቸው አይቀሬ ነውና!

# ማስጠንቀቂያው

**'ካከረሩት ይበጠሳል።'** እንዳይኾን በግልጽ እንደሚታወቀው የምእመናኑ ክፍል በታላቅ ትእግስትና አስተዋይነት ጉዳዩን በጠበቃ ይዞ እያስታመመ ይዟል። በኛ በኩል ቁልፉን ካስረከቡን የሕጉን ጉዳይ እናግደዋለን። አንድ እሁድ በዚህ የከፋ ውርጭ ገረገራው ላይ ጸልዮ እንዳይበታተን እህቶች ባዘጋጁልን ቡና ሻይ የነበረው 182 ምእመን "እናዋጣ ! እናዋጣ!" ብሎ ወደ አሥር ሺህ ፓውንድ የሚጠጋ አዋጣ። የሕግ ጉዳይ ውድነቱ ቢታወቅም ሕንጻ ቤ/ክንን በምንም ገንዘብ ምክንያት ለጠላት አትተላለፍብንም ብሎ ቆርጦ ተነስቷል። በዚህ ዓይነት ንብረቱን ሲያስመልስ ለዚህ ውርጭ-ውርድትና ሕመም የዳረገውን በመልካም ያየዋል ማለት ዘበት ነው። በዚያን ዓይነት የተሳሳቱትማ ---ቢለድፉባቸው፦ ልብሶቻቸውን በቀለማት ቢያሳምሩላቸው ይደነቃል? 'ምከረው - ምከረው፦ እምቢ ካለ …' የሚባለው እንዳይደርስ ጆሮ ያለው ይስማ!

**<u>በምንም! በምንም! በምንም! ዓይነትና ዘዴ ብቸኛዋን የጸሎት ቤታችንን ለጠላት ተላልፋ እንድትሰጥ አይደረግም። መታሰቡም የድፍረት ድፍረት ነው!!!</u>**

## <u>ውጪ ላለነው ስደተኞችኹሉ ማሰባሰቢያ!</u>

አሜሪካን እንዲህ ዓይነቱ ወንጀል ሳይደጋገም አልቀረም። ከንግዲህ ካለፈው ተምረን እንዴት እንደምናስቆመው ምክር መጀመር የግድ ይላል። መረዳዳትም ካለ ወደኋላ ማለት የለም። በራችን ክፍት ነው!! በቀደምት የምንስማማው

***<u>"ሃይማኖታቸውን በጥቅም የለወጡትን፡ መሐላቸውን ያፈረሱትን፦ በጠላት መሣሪያነት ስደተኞችን በገንዘባቸው የገዙትን/ያሠሩትን አብያተ ክርስቲያናትን ከነምእመኑ አሳልፈው የሸጡትን እተወለዱበት ከተማ በሚቆመው ገበያ ላይ የለበሱትን የክህደት ካባና የጫኑትን ማስመስያ ቆብ በውርደት ይገፈፉሉ!"</u>***

***<u>አፈጻጸሙ፦ አገር ለዚህ ሳትመች</u>***

***<u>፩- ቢሞቱ</u>***

***<u>፪- ወጪ ቢኖሩ ውሳኔው ይፈጸማል</u>***

***<u>ለዚህ ትግል ተቃዋሚ ፖ/ፓርቲዎች የቀደምት ኃላፊነት አለባቸው</u>***

ይህ ቀደምት መስማሚያችን ኾኖ ዝርዝሩን ወደፊት በውይይት እናጠነክረዋለን።

**ተጨማሪ፦ የቀድሞው አለቃ፡ ድንገት "እንዴት የቀድሞው! እባላለሁ ቢሉ ከላይ ሮሜን ያንብቡ። ከዚያም**
**መንግሥቱ አገር ጥሎ ከሄደ በኋላ የኢ.ት.ፕሬዜዳንት ነኝ ይላል? ርስዎስ ከቆለፉ በኋላ! እንዴት?!!**